## እርሰዎ ማወቅ **ያለብዎ ነገር**

### መረጃ ስለ **ቲቢ**

ሳንባ ነቀርሳ (ቲቢ) ማይኮባክቴሪየም ቱበርክሎሲስ (M. tuberculosis)በተባለ ባክቴሪያ የሚመጣ ተላላፊ በሽታ ነው። በዋነኛነት ሳንባን የሚያጠቃ ህመም ቢሆንም ማንኛውም የሰውነት ኣካልም ሊያጠቃ ይችላል። አንድ የሚታይ ወይም ንቁ የቲቢ በሽታ ያለበት ሰው ሲሰል፣ ሲሰቅ፣ ሲያስነጥስ ወይም ሲዘፍን በአየር በሚሰራጭ ባክቴሪያ አማካኝነት የሚተላለፍ ነው። ቲቢ በአብዛኛው የዓለማችን ክፍል ዋነኛ የህመም እና የሞት ምክንያት ነው። በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ እና በውጭ ቲቢን ለማጥፋት ቀጣይነት ያላችው ጥረቶች መደረግ አለባቸው።

አንድ በቲቢ የተያዘ ሰው በሽታውን ወደ ጓደኞቹ፣ ቤተሰብ፣ የስራ ባልደረቦች እና አብረው የሚማሩ ሰዎች ሊያስተላልፍ ይችላል። ቲቢ ከባድ እና ለሞት የሚዳርግ ሊሆን ይችላል። ጥሩ ነገሩ ግን ቲቢን በህክምና መከላከል ይቻላል።

### ስለ **LTBI (ድብቅ የ ቲቢ በሽታ)**

latent tuberculosis infection (LTBI) (ድብቅ የቲቢ በሽታ) ያለባቸው ሰዎች በ M. tuberculosis በተባለው ባክቴሪያ የተያዙ ሰዎች ናቸው። አንዳንድ የቲቢ ባክቴሪያ በሰውነታቸው የሚገኛባቸው ሰዎች የሚታይ ወይም ንቁ የቲቢ በሽታ ፈጽሞ ላይታይባቸው ይችላል። አንዳንድ ሰዎች፣ በተለይም ደግሞ የተዳከመ የሰውነት በሽታ የመከላከል አቅም ያላቸው እና ሌሎች ለአደጋ አጋላጭ ሁኔታዎች ያሉባቸው ሰዎች የሚታይ ወይም ንቁ የቲቢ በሽታ ሊታይባቸው ይችላል።

LTBI (ድብቅ የ ቲቢ በሽታ) ያለባቸው ሰዎች ህመም አይሰማቸው፣ በዚህም የተነሳ ባክቴሪያው በውስጣቸው እንዳለ ላያውቁ ይችላሉ። ምንም ዓይነት ምልክት አያሳዩም። በሽታውን አያስተላልፉም። ይሁን እንጂ ድብቅ የነበረው የ ቲቢ በሽታቸው ወደ እሚታይ (ንቁ) የቲቢ በሽታ ከተቀየረ፣ ህክምና ባልተደረገበት ሁኔታ፣ ሊታመሙ እና በሽታውን ወደ ሌሎች ሊያስተላልፉ እና ሊሞቱም ይችላሉ።

### ተጨማሪግብዓቶች


Centers for Disease Control and Prevention (የበሽታ መቆጣጠሪያ እና መከላከያ ማዕከላት)። (2012)። የሳንባ ነቀርሳ (ቲቢ):- እውነታዎቹን ይወቁ! [ብሮሸር]። https://www.cdc.gov/tb/publications/pamphlets/Tuberculosis_Get_the-facts.pdf

Centers for Disease Control and Prevention, National Center for HIV/AIDS, Viral Hepatitis, STD, and TB Prevention (ብሄራዊ የኤች ኣይ ቪ/ኤድስ ፣ ተላላፊ ሄፓታይተስ፣ የአባለዘር በሽታ እና ቲቢ መከላከል ማዕከላት)። (2014)። ሳንባ ነቀርሳ [ቲቢ] ን የተመለከቱ ጥያቄዎች እና መልሶች። https://www.cdc.gov/tb/publications/faqs/pdfs/qa.pdf

Centers for Disease Control and Prevention (የበሽታ ቁጥጥር እና መከላከል ማዕከላት)፣ National Center for HIV/AIDS፣ Viral Hepatitis፣ STD፣ and TB Prevention (ብሄራዊ የ ኤች ኣይ ቪ/ኤድስ ፣ ተላላፊ ሄፓታይተስ፣ የ ኣባላዘር በሽታ እና ቲቢ መከላከል ማዕከል)። (2014). ቲቢ፤ ስለ ሳንባ ነቀርሳ በሽታ እርሰዎ ማወቅ ያለብዎ ነገሮች። https://www.cdc.gov/tb/publications/pamphlets/tb_infection.pdf


**Latent TB. Active Concern.**
**Tuberculosis Program**


Virginia Department of Health
(የቨርጂኒያ ጤና መምሪያ)
**ስልክ**:- 804-864-7906
**ፋክስ**:- 804-371-0248 or 804-416-5178
**ኢሜይል፤** tuberculosis@vdh.virginia.gov
**ድረ-ገጽ፤** www.vdh.virginia.gov/tuberculosis/


VIRGINIA DEPARTMENT OF HEALTH

Virginia Department of Health TB Program (የቨርጂኒያ የጤና መምሪያ የቲቢ ፕሮግራም) ሁሉም በቨርጂኒያ የሚኖሩ ሰዎች ጤና እና ደህንነታቸውን ለመጠበቅ ቲቢን ለመከላከል፣ ለማከም እና ለማስወገድ ይሰራል።


ዲዛይን በቨርጂኒያ DGS፣ በግራፊክ ኮሙኒኬሽን ጽህፈት ቤት:- የግዢዎች እና አቅርቦት ክፍል




ገምግም • መርምር • አክም

# LATENT TB (ድብቅ ቲቢ)። አሁን ላይ ያለ ሰጋት።



በድብቅ የቲቢ በሽታ መያዝ መሰረታውያን

የሳንባ ነቀርሳ (ቲቢ) ፕሮግራም
Virginia Department of Health
(የቨርጂኒያ ጤና መምሪያ)

# እርሰዎ ማድረግ የሚችሉት ነገር

## I. ይገምግሙ

### በ Latent TB(ድብቅ ቲቢ) የመያዝ አደጋ ላይ መሆን አለመሆንዎን ይለዩ

**የሚታይ ወይም ንቁ ቲቢ በሰፋት ሊገኝበት በሚችል ትልቅ የሰዎች ሰብሰብ ውሰጥ ነው የሚኖሩት፡ ማለትም በከሚከተሉት ውሰጥ፡**

- የቤት አልባ ሰዎች መጠለያ
- የማረሚያ ቤት
- የማስታመሚያ ቤት (Nursing home)

**እርሰዎ በሚከተሉት ምክንያቶች የተነሳ የተዳከመ የሰውነት የበሽታ የመከላከል አቅም አልዎት:-**

- ኤች አይ ቪ
- የኣካል ክፍል ንቅለ-ተከላ
- በሚወሰዱት መድሃኒት

**ከአንድ የሚታይ ወይም ንቁ የቲቢ በሽታ ካለበት ሰው ጋር ጊዜ አሳልፈው ከሆነ**

**በመርፌ የሚሰጡ መድሃኒቶች ይወሰዳሉ**

**የሚከተሉትን የመሰሉ የሚታይ ወይም የንቁ ቲቢ ምልክቶች አሉብዎት:-**

- ከሶሰት ሳምንታት በላይ የቆየ ሳል
- ትኩሳት
- የደረት ህመም
- የክብደት መቀነሰ
- ሌሊት ላይ ማላብ
- ድካም
- የምግብ ፍላጎት መቀነሰ

**እርሰዎ በሚከተሉት የሚታይ ወይም ንቁ የቲቢ በሽታ በተሰፋፋባቸው ቦታዎች ላይ ተወልደዋል፣ ከወር በላይ ለሆነ ጊዜ ቆይተዋል ወይም በተደጋጋሚ ጉዞ አድርገዋል፡-**

- አፍሪካ
- ኤሽያ
- ሜክሲኮ
- ማዕከላዊ አሜሪካ
- ደቡብ አሜሪካ
- ካሪቢያን
- ምሰራቃዊ አውሮፓ

**በዩናይትድ ሰቴትሰ ውሰጥ ከ 80% በላይ የሚሆኑት በሚታይ ወይም ንቁ ቲቢ የሚጠቁ ታማሚዎች ያልታከመ latent TB(ድብቅ ቲቢ) ነበረባቸው።**

## II. ምርመራ

### የቲቢ ምርመራ ለማድረግ ጥያቄ ያቅርቡ

#### የቲቢ ምርመራ አማራጮች

የህመም ሰሜት ባይኖርብዎትም LTBI (ድብቅ የቲቢ በሽታ) ሊኖርብዎ ይችላል። ከዚህ በፊት የተገለጹት ለአደጋ አጋላጭ ምክንያቶች አንዳቸውም ያሉብዎ ከሆነ፣ የቲቢ ምርመራ ለማድረግ አንድም ዶክተርዎን ወይም በአከባቢዎ የሚገኘን የጤና መምሪያን መጠየቅ አለብዎ። የደም ወይም የቆዳ ምርመራ ማድረግ ይችላሉ፣ ሁለቱም ምርመራዎች ህመም የሚያሰከትሉ አይደሉም። በምርመራ በሽታው እንዳለብዎ ከተረጋገጠ፣ ያለብው የሚታይ (ንቁ) ቲቢ ነው ወይሰ በድብቅ ያለ መሆኑን ለመለየት ዶክተርዎ የደረት ራጅ እንዲነሱ ያዝልዎታል። የምርመራ ውጤትዎ አሉታዊ (ኔጋቲቭ) ከሆነ እና የተዳከመ የሰውነት በሽታ የመከላከል አቅም ካልዎት ወይም በቅርቡ ታመው ከነበረ፣ ዶክተርዎ ሌላ ምርመራ ሊያዝ ይችላል።

#### የቲቢ ምርመራ እና የቢሲጂ (BCG) ክትባት

በአንዳንድ የሚታይ ወይም ንቁ ቲቢ በሰፋት በሚታይባቸው ሃገሮች፣ የመከላከያ ከትባትé ቢሲጂ (BCG) ለጨቅላ ህፃናት እና ለትንሽ ልጆች ይሰጣል።  ይህ በዩናይትድ ሰቴትሰ ውሰጥ የተለመደ አይደለም ይሁን እንጂ በሌላ ሀገር የተወለዱ ከሆነ በልጅነትዎ ጊዜ የቢሲጂ ክትባት ተከትበው ሊሆን ይችላል።

ሁኔታው ይህ ሲሆን፣ የ latent TB (ድብቅ የቲቢ በሽታ) ምርመራ በሚያደርጉበት ጊዜ የደም ምርመራ ማድረግ በጣም ተመራጭ ነው።

**የቢሲጂ ክትባት ተከትበው ከሆነ የቲቢ የደም ምርመራ በመጠቀም ምርመራ ማድረግ አለብዎ። በቲቢ ባክቴሪያ ያልተጠቁም ቢሆን እንኳን የቆዳ ምርመራ ማድረግ አወንታዊ (ፖዘቲቭ) ምላሽ ሊያሰገኝ ይችላል**



## III. ህክምና

### ሙሉ ህክምና

#### ህክምና

latent TB (ድብቅ የቲቢ በሽታ) እንዳለብዎ በህክምና ከተረጋገጠ፣ ብዙ በአማራጭነት ሊቀርቡ የሚችሉ ህክምናዎች አሉ።  ዶክተርዎ የሚታይ ወይም ንቁ የቲቢ በሽታ የመታመም ዕድልዎን የሚቀንሱ መድሃኒቶች ያዝልዎታል። ያሰታውሱ፣ ወደ ሚታይ ወይም ንቁ የተቀየረ ቲቢ ብቻ ነው ሊተላለፍ የሚችለው፣ ሰለዚህ latent TB (ድብቅ የቲቢ በሽታ) አለብዎ ማለት ቤተሰብዎን እና ጓደኞችዎን ለአደጋ ይዳርጋሉ ማለት አይደለም።

በምርመራ latent TB (ድብቅ የ ቲቢ በሽታ) እንዳለብዎ ከተረጋገጠ በኋላ ወዲያው ህክምና ማግኘትዎ እጅግ አስፈላጊ ነው። ራሰዎን ከበሽታ የሚከላከሉበት ምርጡ መንገድ ሁሉንም የታዘዘልዎን መድሃኒት መጨረሰ ነው። የቲቢን ባክቴሪያ የማሰወገጃው ምርጡ መንገድ የ ቲቢ መድሃኒት መውሰድ ነው። ህክምናውን አሰቀድመው ካቆሙ ወይም መድሃኒት የሚወሰድበትን ጊዜ ከዘለሉ፣ የቲቢ ባክቴሪያ ሰውነትዎን ሊያሸንፈው ይችላል።

#### ከህክምና በኋላ

ህክምናውን ከጨረሱ በኋላም ቢሆን፣ በቀጣይ በምርመራ በሽታው ሊገኝብዎ ይችላል። ሙሉ የህክምናውን ቆይታ እንዳጠናቀቁ የሚገልጽ የጽሑፍ ማሰረጃ እንዲሰጥዎ ዶክተርዎን መጠየቅ አለብዎ። እና መጥፎ ነገሩ ደግሞ ወደ ፊት እንደ አዲሰ ከተጋለጡ በቲቢ ሊያዙ ይችላሉ። የሚወሰዱት መድሃኒት በዚያን ሰዓት በሰውነትዎ ውሰጥ ያለውን ባክቴሪያ ብቻ ነው የሚያሰወግደው።

**LTBI (ድብቅ የቲቢ በሽታ) በፍጥነት ሊታከም ይችላል። ህክምናው ከ 3-4 ወራት ሊወሰድ ይችላል።**

ተጨማሪ ጥያቄዎች ካልዎት፣ እባክዎን
Virginia Department of Health TB Program
(የቨርጂኒያ የጤና መምሪያ የቲቢ ፕሮግራምን)ን ያነጋግሩ።